# የወጣቶች የፆታ እኩልነት በኢትዮጵያ

*November, 2019*

JOHNS HOPKINS
BLOOMBERG SCHOOL of PUBLIC HEALTH
Population, Family and Reproductive Health

GEAS

POPULATION COUNCIL
Ideas. Evidence. Impact.





# የወጣቶች ቁጥር በኢትዮጵያ

አንድ አራተኛው /23/ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ወጣቶች ሲሆኑ እድሚያቸው ከ10-19 ዓመት ይፈረጃል[1]። አብዛኞቹም /81%/ የሚኖሩት በገጠር አካባቢ ነው[2]። ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ኢትዮጵያ በየወጣቶች ብዛት እና የህዝብ ቁጥር የሚሰጣትን እድል መጠቀም የምትችልበት እድል የሚፈጠረው በ2040[3] ነው። እንደሚታየውም ከፍተኛው የወጣቶች ብዛት እና የፆታ እኩልነት አለመኖሩ እነዚህን ጉድለቶች ተረድቶ ለማሟላት ስልት መፈለጉ ወሳኝ ነው።

ጎልቶ የሚታይም መሻሻል እና አመቺ ሁኔታ መፈጠሩ መካድ አይቻልም ምክንያቱም የኢትዮጵያ ማህበረሰብ የፆታ እኩልነትን ለማስፈር አሉታዊ ጥረት እያደረገ ነው።
በዋነኝነት የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዚዳንት[4] መሾም እንዲሁም የካቢነው በ2018 50/100 ሴቶች መሆናቸው[5] የፆታ እኩልነት ሊሆን የሚችል በቅርብ ቀን የሚሳካ ራዕይ ያደርገዋል። የዘሬ ህፃናትም የነገ ወጣቶች የሚሆኑበት ቀን ይቃረባል፣ ሳንናገር ማለፍ የማንችለው በቅርብ እንደሰማነው ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አሊ የ2019 የሰላም ሽልማት ባገኙበት ጊዜ አንደኛው መሰፈርቱ የጠቀሰው ሴቶች በኢተዮጵያ ፖለቲካም ሆነ በማህበረሰብ ኑሯቸው ሚናቸው እንዲጎላ ማስ።

# በትምህርት ዓለም ውስጥ የፆታ እኩልነት መሳካት

- አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚመዘገቡት ተማሪዎች ወንዶችና ሴቶች መካከል ሲተያይ እኩልነትን ይቀርባል። ከአንደኛ ደረጃ በኋላ የሚማሩ የሴት ቁጥሮች እጅግ ይቀንሳል[3,6]። እኩልነት ቁጥር ለመጥቀስ በሁለተኛ ደረጃ እኩልነት “index” 0.7 ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሲሆን ደግሞ በግማሽ ተካፍሎ 0.43 ያሽቆለቁላል። ይህም የሚያመላክተው ወንዶች ከዩኒቨርሲቲ የመመረቅ እድላቸው ሁለት እጥፍ ነው[3]።

- እድሚያቸው በጨመረ ቁጥር ወንዶችም ሆነ የሴቶች ምዝገባ እየቀነሰ ቢሄድም ነገር ግን በከፍተኛ ቁጥር በከፍተኛ ቁጥር ትምህርት የሚያቋርጡት ግን 15-16 የሞላቸው የገጠር ሴቶች ናቸው[6]።

- የወጣቶች በትምህርት መገለጥ እንዳሉበት አካባቢ ይወሰናል። 10-14 ዓመት የሞላቸው ታዳጊዎች መካከል 90 በመቶ የከተማ ነዋሪ ወንዶች እንዲሁም 93 በመቶ የከተማ ነዋሪ ሴት ልጆች ትምህርት ይማራሉ። በዛው እድሜ የሚገኙ 77 በመቶ የገጠር ተወላጅ ወንዶችና 78 በመቶ የገጠር ተወላጅ ሴቶች ትምህርት ይማራሉ[6]።

- ጎልቶ የሚታየው የፆታ ሁኔታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን ለመማር የወጣቶች የሚቃረቡበት እድሜ ሲሆን ይህም ክስተት ይበልጥ የሚታየው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ነው። ከ20 ተማሪ 17 ወንድ 3 ሴት የሚሆነበት አማካኝ ውጤት ነው ያለው። የሴት አርዓያዎች መጉደል እንዲሁም ወንዶች የበላይ የሆኑበት አካባቢ መሆኑ ለሴቶች እንደማይመቻቸው ግልፅ ነው። ይህም ሴቶች ሳይንሰና ቴክኖሎጂ እንዳይማሩ ያግዳቸዋል[7]።

- የኢትዮጵያ የትምህርት ሲስተም ሴቶች ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ለማበረታታት ዩኒቨርሲቲ ሚገቡበትን ነጥብም ዝቅ በማድረግ ይተባበራቸዋል፣ ነገር ግን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአብዛኛው ከከተማ የመጡ ወንድ ልጆች ናቸው[8,9]።

- ሴቶች በሁለተኛ ደረጃ የሚማሩ የሴት ልጆች ቁጥር መቀነስ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት ቁጥር መመንመን ከፆታ መስፈርቶች ጋር የተቆራኘ ነው። ብዙ ሴቶች በይበልጥም የገጠር ልጆች በእንጭጭ እድሜ ስለሚያገቡ እና/ወይንም ከባድ የቤትን ስራ ጫና ስለሚሸከሙ ለትምህርት እና ለጥናት የሚያስፈልገው ኃይልና ጊዜ ይሻማባቸዋል። ሌሎች ደግሞ ቤተሰቦቻቸው 1 በትምህርት ቤት ርቀት 2. በደህንነታቸው በመስጋት እንዲሁም በድህነት ምክንያት የሴቶችን መማር ዋጋ አይሰጡትም[10]።

- አንድ ጥናት  እንዳመላከተውም አንድ የተለመደ ተደጋጋሚ ድርጊት አጉልቶ ሊያወጣ ችሏል። ይህም ትምህርት ከሚመዘገቡ ሴቶቸ መካከል ከ7 እስከ 14 ዓመት የሞላቸው ከወንዶች ይልቅ ከፍ ያለ የተለመደ ነገር ይታይባቸዋል። ይህም (path dependency) ማለትም አንድ ልጅ አምና ትምህርት ካቋረጠ በአሁኑ ዓመት ትምህርት የመቀጠል እድል የመነመነ ክስተት ነው። ተመራማሪዎች እንደሚሉትም ይህ የተለመደ ክስተት የሚያሳየው ብዙ ጊዜ ሴቶች ትምህርት የሚያቋርጡት እንደጋብቻ ዓይነት ቋሚ ለውጥ ሲያጋጥማቸው ሲሆን ወንዶች ግን በጊዜያዊ ችግር ያቅም ማነስ ምክንያት ትምህርት ቢያቋርጡም መልሰው ትምህርት ይጀምራሉ[11]።

*The reasons behind the steep declines in girls’ attendance in secondary school and extremely low enrollment in tertiary school are grounded in gender norms.*

# የፆታ እና የስነተዋልዶ ጤና አቅርቦት እኩልነት

- ከ15 እስከ 19 ላሉ ሴት ወጣቶች ኢትዮጵያ ከ1000ዎች 79 እንደሚወልዱ አሳውቃለች[19]።
  - የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ ወጣቶች ቁጥር አነስተኛ ነው። ከ15 እስከ 19 ዓመት ከሞላቸው ያገቡ ሴቶች መካከልም ከሶስት ሴት አንዷ ብቻ የወሊድ መቆጣጠሪያ ትጠቀማለች[14]።
  - ያላገቡ ነገር ግን የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ የጀመሩ እድሜያቸው ከ15-19 ያሉ ሴቶች ግን 59 በመቶ የወሊድ መከላከያ ይጠቀማሉ። ነገር ግን ይህ ጥናት የተደረገው በተወሰነ የማህበረሰቡ ናሙና ላይ ነው[14]።
  - በአማካኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርጉ ሴቶች እድሜያቸው ከ20 እስከ 24 ላሉ ሴቶች 18.6 ሲሆን በ5 ወር የመጀመሪያ ጋብቻቸውን ከሚፈጽሙ ሴቶች ያንሳል። ይህም ከ20 እስከ 24 ዓመት ለሞላቸው ሴቶች 19 ዓመት ነው[14]።
  - 10 በመቶ ሴቶች 18 ዓመት ሲሞላቸው ያገቡ ሲሆኑ 24 በመቶዎቹ 5 እድሜ ሳይሞላቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ። 62 በመቶዎቹ 18 ሳይሞላቸው፣ 76 በመቶዎቹ 20 ዓመት ሳይሞላቸው ግብረ ስጋ ፈጽመዋል[14]።
  - ባለፉት አመታትም ከ2000-2016 ባለው ጊዜ ውስጥ 18 ዓመት ሳይሞላቸው በፊት ግብረ ስጋ የሚፈፅሙ ሴቶች በ7 በመቶ ሲቀንስ ይህም የጋብቻ እድሜያቸው ያንፀባርቃል[14] ።
  - ትምህርት ባቆሙ እንዲሁም ከ10 እስከ 19 በሞላቸው የከተማ ሴቶች ያተኮረ ጥናት እንዳሳየው ከ4 አንዷ ግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽመዋል። ከእነዚህ ሴቶች መካከልም 1/3 እንደተናገሩት ተታለው ወይንም ተገደው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል[20]።
  - ወንዶች ሲያገቡም ሆነ የመጀመሪያ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ እድሜአቸው ከፍ ያለ በቁጥር ለማስቀመጥም 15 ዓመት ሳይሞላቸው የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙ ወንዶች 2 በመቶ ናቸው። 17 በመቶዎቹ 18 ዓመት ሲሞላቸው 36 በመቶዎቹ 20 ዓመት ሲሞላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል[14]።
  - ወንዶች በአማካኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ግብረ ስጋ ግንኙነት 21.2 ዓመት ሲሞላቸው ሲሆን በአማካኝ ከሚያገቡበተ 2.5 አመት በፊት ነው[14] ።
- ሴቶች ለመጀሚያ የሚወልዱበት እድሜ በአማካኝ 19.2 እድሜ ሲሆን ከኢትዮጵያዊ ሴቶች መካከል ግማሹ 20 ዓመት ሳይሞላቸው ይወልዳሉ[14] ።
  - እርግጥ ከ2000-2016 ባለው ጊዜ የተወሰነ መሻሻል ይታያል። ከ15-19 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆች መካከል ወይ አርግዘዋል ወይ የመጀመሪያ ልጃቸውን ወልደዋል። ከ2000 ዓ.ም ጋር ሲተያይም 13 በመቶ 16 ዓመት ጨምረው አርግዘዋል ወልደዋል[14]።
  - ገጠር የሚኖሩ ሴቶች 18 ዓመት ሲሞላቸው የመውለድ እድላቸው ሁለት እጥፍ ሲሆን /28/ ከተማ ያሉ ሴቶች 11 በመቶ ናቸው14 ። ይህ ማለትም ሁለተኛ ደረጃ የተማሩ ሴቶች ካልተማሩ ሴቶች ሲተያዩ የሚወልዱበት እድሜ 6 ዓመት ይጨምራል። /24.5 ዓመት - 18.5 ዓመት/[14]
- በተለየ ሁኔታ ወጣት ሴቶች ስለ አፍላ እድሜ፣ ስለ ፖርምስና፣ ስለ ወር አበባና ስለ ወር አበባ ንጽህና አጠባበቅ የሚያገኙት ምክር ወይም መረጃ የተወሰነ ነው። በተለምዶ የወር አበባ የተንቋሸሸ እና ብዙ ጊዜ አንድ ሴት ለጋብቻ መድረሷን የሚያሳይ ነገር ነው12። ይህ ማለትም ሴቶች አፍላ እድሜ ላይ ሲደርሱ ሴቶች ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ የሚያሰናክል ነው። ምክንያቱም 15 በመቶ ሴት ልጆች ወይንም ወጣቶች እንደተናገሩት በወር አበባቸው ምክንያት ትምህርት ቤት ቀርተዋል[6]።

**ሴቶች ወደ ከተማ የሚጎርፉበት ምክንያት አንዱ ያለ እድሜ ጋብቻ ነው። በኢትዮጵያ ገጠሮች ውስጥ ሴት ልጆች የሚዳሩት ገና ህፃን ሆነው ነው። ሴቶች ይህን ይጠሉታል በተጨማሪም ብዙ ሰዎች የሚኖሩት በድህነት ነው። ሴቶቹ ደግሞ በመሰደድ ቤተሰብን ለመርዳት ይሞክራሉ። ለነዚህ ሁለት መክንያቶች ነው ሴቶቹ ሚመጡት ።**

ፍቃድ የሌለው በመተማ የሚኖር ደላላ እድሜው 32 የዘጠኛ ዓመት ትምህርት ያለው


“የወጣት ሴቶቾን አካል ብልጽግና እና የፆታ ፍትህን ከሚያጨናግፉ የተለመዱ ድርጊቶች መካከል፡ ያለ እድሜ የሚፈጸም ጋብቻ እና እርግዝና ይጠቀሳል። የቤት ውስጥ ኃላፊነቶች ጫና መሸከም፣ በነፃነት መንቀሳቀስ አለመቻል፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ግንኙነቶች ከወንድነት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጥቃቶች፣ /በቤት ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ/ ያላቸውም ተቀባይነት ውሳኔ መውሰድ አለመቻል ስለ ስነ ተዋልዶ ወይንም ፆታዊ ውሳኔዎች መቆጣጠር አለመቻል /ከነዚህ መካከልም በአብዛኛው ማህበረሰቦች ከሴቶች ግርዛት መጋለጥን ያካትታል/ ቤተሰብ ውስጥ የተሰሚነት ማነስ እና ለወንዶች የሚያዷሉ የእንክብካቤ ልምዶች ሚጠቀሱ ናቸው[21]። “

- ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው እርጉዝ ሴቶች መካል ከ15-24 ዓመት መካከል የሚገኙት ባልተፈለገ እርግዝና ምክንያት ችግር ይገጥማቸዋል። በዚ ጊዜም ከጋብቻ በፊት በፍላጎትም ሆነ በግዳጅ ግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ ነው። ለህገወጥ ውርጃም ይጋለጣሉ። ግንኙነትን ከሚፈጽሙ ከተለያ የማህበረሰቡ አካላት መካከልም ውርጃ ከሚፈጽሙት አብዛኛው ወጣት ሴቶች ናቸው። 19.6 ለ 1000 ሴት22። ህጋዊ ውርጃ ሴቶች ናቸው። ይህም ግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ በጀመሩ ወጣቶች ዘንድ የእርግዝና እና ከፍ ያለ የውርጃ ቁጥር የሚያመላክተውም ወሊድ መቆጣጠሪያ ማግኘት አዳጋች መሆኑ ነው።

- ከበሽታ መተላለፍ ጋር ተያይዞ 15-24 ዓመት የሞላቸው 0.2 በመቶ ወጣቶች ኤች አይ ቪ positive ናቸው። በዚህ እድሜ ከሚገኙ ወጣቶችም ኤች አይ ቪ ለሴቶች ሶስት ጊዜ እጥፍ ከወንዶች ከፍ ይላል /0.3-0.1/23 ለዚህም ምክንያቶች አንዳንዶቹም ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለ እውቀት ማነስ በፆታ ግንኙነቶች ውስጥ ያለ አቅም ማነስ የፆታ ጥቃት ሴተኛ አዳሪነት ወይንም ፆታዊ የንግድ ብዝበዛ ይጠቀሳሉ[10]።

**PREVALENCE OF FGM IN ETHIOPIA BY REGION [25]**

[Data source DHS 2016]
©28 Too Many




## የሴት ልጅ ግርዛት

- 23-8 ሚሊየን ሕፃናትና አዋቂ ቶች የተገረዙባት ኢትዮጵያ ከግብፅ ቀጥሎ ሁለተኛ ቦታ ላይ ትገኛለች34። ከ15 እስከ 19 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆች መካከል 47% ተገርዘዋል። አብዛኛውን ጊዜም አምስት ዓመት ያልሞላቸው ህፃናት ህፃናት ለብዛት ይገረዛሉ14። ከ14 ዓመት በታች ካሉት ታዳጊ ሕፃን ሴቶች መካከልም 16% ተገርዘዋል። ባጠቃላይ 28% እድሜያቸው ከ10-14 ያሉ ሴት ልጆች ይገረዛሉ[14]።

- ከ2004 ጀምሮ ይህ ጎጂ ልማድ በህግ ተከልክሏል። ከ2005-2016 ባለው ጊዜ ከ15-19 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆች ዘንድም ድርጊቱ በ24 በመቶ ቀንሷል። ነገር ግን የቀነሰው በእውነትም ሰዎች ድርጊቱን አቁመው ይሆን ወይም በህግ ሰለተከለከለ እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም[14]።

- አንዳንድ ዘገባዎች እንደሚያመላክቱት ጠንካራ የህግ ድጋፍ የሰዎችን ድርጊትና አስተሳሰብ ቀስ በቀስ ለመለወጥ ችሏል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ደጋፉ የመነመነ እና ስለ ግርዛት ያለውን ህግ በተመለከተ ያለው ዕውቀና ውስን ሞኑን ይናገራሉ።

    - እነዚህ ልዩነቶች ከክልል ክልል የግርዛት መፈጸም ሁኔታ ስለሚለያይ ሊሆን ይቸላል[25]።

# የኃይል ጥቃት[26]

- በቅርብ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ከ10-12 ዓመት የሞላቸው ወጣቶች ቤታቸው ውስጥ የኃይል ጥቃት ይገጥማቸዋል ወይ ያያሉ።
  - ሴት ልጆች ለወላጆች ሲቀጡ በብዛኛው የፆታዊ ሚናን ባለማክበር ወይም ከሴት ልጅ ባህሪ የሚጠበቁ መስፈርቶችን ባለማሟላታቸው ነው። ለምሳሌ:- የቤት ውስጥ ስራ ላይ ጥፋት ለመፈፀም /ይህም ደግሞ በተለምዶ የሴት ልጅ ዋና ሞያ ቤት ውስጥ ስራ መስራት ነው ተብሎ ስለሚጠበቅ ነው።/
  - የወላጆቻቸውን ቅጣት ቢፈሩም ለአብዛኞቹ ወጣቶች መገረፍ ወይም መመታት የተለመደ ነው።
  - በታላቅ ወንድም ወይም እህት መመታት የወላጆችን ቅጣት ከመደገም ጋር ይያያዛል።
- በትምህርት ቤት ውስጥ 78% ወንዶች ተመትታው እንደሚያውቁ ይናገራሉ 66% ሴት ልጆች መመታታቸውን ይናገራሉ። ነገር ግን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ሴቶች በብዛት የሚቀጡት ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ነገር ነው። ይህም ክፍል ውስጥ በመሳሳት ወይም ቤት ውስጥ ስራ በዝቶባው ትምህርት ቤት አርፍደው በመድረሳቸው ነው።
  - ትምህርት ቤት አስተማሪ ሲቀጣቸውም ወላጆች ዳግም መቅጣታቸው የተለመደ ነው።
  - ብዙ ወጣቶች በአካላዊ ጥቃት ምክንያት ትምህርት ያቋረጠ ሰው ያውቃሉ። አብዛኞቹ ግን በዛው ልክ ተማሪ በሚበዛባቸው ክፍሎች ውስጥ መጋረፍ እና መማታት አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ።

> **“ሰፈር ውስጥ ጉልበተኛ ነኝ ወንዶች ሲተናኮሉኝ እደበድባቸዋለሁ ሀይለኛ ነኝ ነገር የሚፈልገኝን ማንኛውንም ሰው መደብደብ እችላለሁ”**
>
> የ11 ዓመት የሞላው የድሬደዋ ልጅ[27]።

> **“ወንድ መሆን ለለብኝ ወንዶች ጎበዝ ናቸው ወንድ መሆን ብችል በጣም ደስ ይለኛ ነበር ወንዶች ጊሊ /ጩቤ/ ተጠቅሞ በመደባደብ ያሸንፋሉ”**
>
> ዞን 5 ማህበረሰብ በሀረር ውስጥ የምትኖር ታዳጊ ሴት ልጅ

> **“አንዳንዴ ወንዶች ኃይል በመጠቀም የግብረ ስጋ ግንኙነት ለመፈጸም ይሞክራሉ እንቢ ያለችም ሴት ትደበደባለች”**
>
> ዞን 5 ማህበረሰብ A አፋር ኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኝ ሴት ልጅ

- ከትምህርት ቤት ውጭ በእኩያማቾቹ መካከል የኃይል ጥቃት አዲስ ነገር አይደለም። ወደ ግማሽ የሚጠጉት (46%) ወጣት ታዳጊዎች ባሳለፉት ዓመት ውስጥ በኩያቸው ጥቃት እንደተሰነዘረባቸው ይናገራሉ። ከሴቶች ሲታይም በወንዶች ላይ ጥቃቱ ይበረታል (52% ለ39%)
  - እኩያማቾች መካከል የሚከሰት ጥቃት የሚፈጸመውም ሆነ የሚያተኩረው ወንዶች ላይ ሲሆን ይህም በማህበረሰቡ ጥንካሬን እና ወንድነትን እንዴት እንደሚያቀራጉት አጉልቶ ያሳያል።
- ከ15-19 ዓመት የሞላቸው 4% ሴቶች ፆታዊ ጥቃት እንዳጋጠማቸው ይናገራሉ። ፆታዊ ጥቃት የሚያጋጥማቸው ሴቶች ብዙ ጊዜ መፍትሄ እንደማያገኙ እና ከአጥቂያቸው በቀልን በመፍራት ቤተሰብም ጥፋተኛ አድርጎ ይወቅሰናል በለው በመስጋት ለቤተሰብ መናገር ያፍራሉ።
  - ሲደፈሩም አንዳንድ ሴቶች የደፈራቸው ሰው እንዲያገቡ ይገደዳሉ ይህም ብዙ ጊዜ የጋብቻ ጥያቄን አልቀበል ሲሉ ይከሰታል።
- በምስራቅ ኢትዮጵያ የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው 764 ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሴቶች መካከል 68% ቢያስ አንድ ጊዜ ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። 52% ቢያንስ አንድ ጊዜ ፆታዊ ተንኮሳ ሲያጋጥማቸው 56% ፆታዊ ጥቃት 25% ጾታዊ ከጿላ 15% ደግሞ ጾታዊ ጥቃት እንዳጋጠማቸው ይናገራሉ[27]።
- በ7 የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ የተደረገ እና 10080 ታዳጊዎች እና ወጣቶችን ያካተተ ጥናት እንደሚያመላክተው 33% ጾታዊ ግንኙነት ከጀመሩ ሴቶች መካከል የመጀመሪያ ጊዜ ግንኙነት ያረጉት በመታለል ወይም በመገደድ ነው: : ይህም ዛቻ ጥቃት ገንዘብ ወይም ስጦታ በመስጠት እና እንቢተኝነትን ባለመቀበል ጭምር ነው። ይህም ጥናት እንዳሳየው 14% ግንኙነተ የጀመሩ ወንዶች የመጀመሪያ ጊዜያቸው በመታለል መሆኑን ይገልጻል[46]።
  - ከፍተኛ የጾታ ጥቃት መኖሩ ሴቶች ትምህርት እንዲያቋርጡ ወይም እንዲያቆሙ ያደረጋል።

[1] ጾታዊ ትንኮሳዎች የሚያካትቱት ያልተፈለጉ ጾታ ነክ ትንኮሳዎች ከወንድ ተማሪ ሲሰነዘሩ ጾታ ነክ ቀልዶችን መስማት ያልተፈለገ እና ቸክ ያለ የግብረ ስጋ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ወሬ ለመስማት መገደድ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፊልም ለወንድ ተማሪ ሲተረክ መስማት አልኮል ለወንድ ተማሪ ጫና መጠጣት እና ወይም ግብረ ስጋ ግንኙነት ባይፈጽሙም ግፊት በወንድ ተማሪ ሲደረግ ነው [27]።

# ወደ ስራ መሸጋገር- ከወጣትነት ወደ አዋቂነት

- የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ የተለመደ ነው። ከ12-14 ዓመት የሚሞላቸው ህጻናት መካከል ከ55% ለስራ መሰማራታቸው ይታወቃል[24]።
- በ7 ክልሎች ላይ የተደረገ እና አፍላ ወጣቶች እና ታዳጊዎች ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያመላክተው። በጣም የተለመደው የቤት ውስጥ ስራ 37% ከተማ ውስጥ ያሉ ሴቶችን ያካትታል ቀጥሎም የጉልት ሸያጭ ስራ 20% ይይዛል ከተማ ከሚኖሩ ወንዶችም የተለመደው ክፍያ የሚያስገኝ ስራ የግንባታ ወይም የቀን ስራሲሆን /22%/ በመቀጠልም ጥቃቅን ንግድ 20% ይይዛል[46]።
- የተሰኘው ጥናት እንደሚያመላክተው በአፍላ አድሜያቸው ሴት ልጆችን የሚሰለጥኑት በይበልጥ የቤት ውጥ ስራ ሲሆን ወንድ ልጆች ግን ወደፊት ስራ ሲያስቀጥር ሙያም እንዲማሩ ይበረታታሉ[28]።
  - ሴት ልጆች እና ወጣት ሴቶች በ1/3 ወይም በግማሽ ከወንዶች ያነሰ ክፍያ ሲያገኙ ከወንዶችም ይበልጥ ያገኙትን ገንዘብ ለቤተሰቦቻቸው ጥቅም እንዲያውሉት ጫና ይደረግባቸዋል[12]።
- ጥናት እንደሚያመላክተው ከ10-14 ዓመት የሞላቸው ታዳጊዎች ከፈተኛ ጉልበት የሚጠይቅ ስራ ይሰራሉ። 67% ወንዶች እንዲሁም 61 ሴቶች ስራ ይሰራሉ ከ15-24 ዓመት የሞላቸው ታዳጊዮች መካከልም 81% ወንዶች እንዲሁም 75% ወንዶች ይሰራሉ[1]።
  - ከሚኖሩበት አካባቢ አኳያ ከ15-29 ዓመት የሞላቸው ታዳጊዎች መካከል 63% የሚሞሉት የከተማ ወጣቶች እንዲሁም 86% የገጠር ወጣቶች የገቢ ምንም የሆነ ስራ ያስራሉ[1]።
- ስራ አጥነትን በተመለከተ ሴቶች ከወንዶች ሶስት እጥፍ ተጋላጭ ናቸው። ከ15-19 አመት የሞላቸውን ሰናይ 50% ሴቶች ወንዶች ደግሞ 14% ናቸው[12]።

# ስደት

- ወጣቶች ወደ አዋቂነት ሲገቡ ከገጠር ወደ ከተማ መሰደዳቸው የተለመደ ነው። በይበልጥም ወደ ከተማ ከሚሰደዱት መካከል 39% ስራ ትምህርት እና የተሻለ እድል ፍለጋ የሚመጡ 19 ዓት የማያልፋቸው ወይም የሚያንሱ ናቸው[29]።
- የሴቶች በሀገር ውስጥ መሰደድ ምክንያት ብዙ ሲሆን ብቻቸውን ወይም ከኩዮቻቸው ጋር መሰደድ፣ በድንገት ለመሰደድ መወሰን ሊያታልሏቸው ከሚችሉ ደላሎች ጋር በመዋዋል /በስደት ጊዜም ሆነ በሰው ቤት በተቀጠሩበት ጊዜ/ 67% የሚሰደድ ሴቶችን ያጋጥማል[30]።
- ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰደዱ ሴቶች አማካኝ እድሜ 14.3 ዓመት ሲሆን ወላጅ የሌላቸው ሴቶች /13.6/ አመት ሲሆናቸው ሁለት ወላጅ ካላቸው ሴቶች /14.6/ አመት በአንድ አመት ያንሳሉ[30]።
- በብዛት በወጣትነት እድሜ ለስደት ከሚገፋፉት ምክንያቶች መካከል የሚጠቀሱት ከገጠር ድህነት ለማምለጥ፣ ችግር፣ በግዱታ በወጣትነት መዳር፣ ከወላጆቻቸው ጋር አለመስማማት፣ በይበልጥም ከእንጀራ አባት ወይም እናት ጋር አለመስማማት ናቸው[30]።
- በስደት ጊዜ ጾታ ያለው ሚና ሲመዘን በ2012 የተካሄደ ጥናት ያመለከተው በአብዛኛው የሚሰደዱት ከ16-20 ዓመት የሞላቸው እና አግብተው የተዳርን ጫና መሸከም ያልቻሉ ሴቶች መሆናቸውን ነው። ከዚህበፊት የተካሄደ ጥናት የሚያመላክተው ይሄ ክስተት ሴት ሕፃናት እና ሴት ልጆች ካልተፈለገ ተዳር ለማምለጥ እንደሚሰደድ አሳይቷል[24]።
- ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ብዙ ሴቶች /በቀበሌ ሰራተኞች በመታገዝ/ እድሜያቸውን በማሳሳት ለስደት የሚያስፈልጋቸውን ሰነድ በእጃቸው ያስገባሉ። ይህ ደግሞ ወጣት ስደተኞችን ለብዝበዛ እና ለጥቃት ተጋላጭ እንዲሆኑ እና በስራ አካባቢያቸው ላይ ተጠቂ ያደርጋቸዋል፡ ፡ በይበልጥም መብታቸውን የማይጠብቅ ኮንትራት በመፈረም፣ ህጋዊ ክትትልም ሆነ ጥበቃ በሌለበት ሁኔታ ዘር ነክ ጻታ ነክ እንዲሁም ሀይማኖትን በተመለከተ ጥቃት እንዲሰነዘርባቸው ያደርጋል[24]።

## GENDER-DISCRIMINATORY POLICIES/NORMS

- አንዳንድ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ ያሉት ደንቦች ሴቶች ወላጅ መሆናቸውን ለማስመስከር ባገቡ ባጭር ጊዜ ውስጥ ማርገዝ አለባቸው ብለው ያስቀምጣሉ። ይህ ማለትም ሴቶች በራሳቸው ወላጅነት ምንም ዓይነት ውሳኔ መወሰን እንደማይችሉ ያሳያል። መንግስት ምንም ያህል የተሻሻሉ ደንባችን ቢደነገግም የስነ ተዋልዶ የወሊድ መቆጣጠሪያዎችን አቅርቦተ ቢጨምርም ሁኔታው ቀጥሏል12። ባል እና ሚስት መካከል ያለ ከፍተኛ የእድሜ ልዩነት ሴቶች ወሊድ የመቆጣጠርም ሆነ ውሳኔ የመወሰን እድላቸውን በይበልጥ ያመነምነዋል በይበልጥም ባሎች እና አማቾች ከጋብቻ ተከትሎ በፍጥነተ እርግዝናን ማየት ሲሹ ሴቶች እና ወላጆቻቸው ግን ላይስማሙ ይችላሉ[47]።

- ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው በ2004 የሴቶች ግርዛት የህግ አንቀጽ 414 ወንጀል መሆኑን ደንግጓል። ይህ ማለትም የሴት ልጅ ግርዛት በህግ ኢትዮጵያ ውስጥ ያስጠይቃል ነገር ግን የህግ አንቀጽ ድርጊቱን ተንትኖ አያስቀምጥም። በተጨማሪም የሴት ልጅ ግርዛት በሚፈጸም ጊዜ ለህግ አለመጠቀምን እንደ ህግ አልተደነገገም። ኬንያ እና ዩጋንዳ ውስጥ እንደተደረገውም ያልተገረዙ ሴቶች እና ቤተሰቦቻቸው ከሚያጋጥማቸው ማግለል እና ማንቋሸሽ ለመጠበቅ የታሰበ ሽፋን የለም[25]።

    - የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስቀጣው ከ3 ወር እስከ 3 ዓመት እስራት እና/ወይም ከ500-10000 ብር የገንዘብ ቅጣት አለው። /አንቀጽ 565፣ 566፣ 567፣ 568/ በተጨማሪም የጾታ ጥቃት /አንቀጽ 564 እና የህጻናት ጋብቻ አንቀጽ 648/ መሰረት እንደወንጀል በህግ ተደንግጓል[25]።

- የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 620 /2/ እና አንቀጽ 626 ሁለቱም ከ13-18 ዓመት እንደ መድፈር ይቀጠራል። ታዳጊው ወይም ታዳጊዋ ፍቃደኛም ቢሆንም በህግ ያስጠይቃል። ኢትዮጵያ ውስጥ ህጋዊ ፈቃደኝነት እድሜ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች ከ18 ዓመት በኋላ ነው[31]።

    - 18 ዓመት ያልሞላቸው ህጻናት በህግ ተቀባይነት የሌው ፍቃድ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ይህን እንደ መድፈር የሚያቀጥረውም ከ18 ዓመት ያልሞላቸው ህጻናት ብስለትም ሆነ የማመዛዘን ችሎታቸው በበቂ መልኩ አልዳበረም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። ልጅ ወይም ልጅቷ ግንኙነት ለመፈጸም ፈቃደኛ ቢሆኑም ህግ ግን የመወሰን መበቱን አያሳጣቸውም [31]።

# በእቅድ መንቀሳቀስ ውጤታማ እንደሆነ ያለ መረጃ

### የኑርዌጃን ቤተ-ክርስትያን እርዳታ ድርጅት እና ሴፍ ዘ ቸልድረን ኢንተርናሽናል የሴቶች ግርዛትን ለማስቀረት ያወጡት እቅድ[24]።

- ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ የተሰፋፋውን የሴት ልጅ ግርዛት ለማስቀረት ሁለት አካላት ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመጣመር ሰውት ያላቸውን ግንዘቤ ለማሳደግ እንዲሁም ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸውን አሰተሳሰብ እና ድርጊቱንም ለመቀነስ በህብረት ሰርተዋል። እቅዳቸውም ያተኮረው ድርጊቱ በከፍተኛ ደረጃ የሚፈጸምባቸው ክልሎች ውስጥ ነው ( በ2005 ዓ.ም) ሱማሌ ክልል (98%)አማራ ክልል (98%) ኦሮሚያ ክልል (97%) አማራ ክልል (89%)ሀረር (100%) ደቡብ ክልል (87%) ነው

- የመጀመሪያው የእቅድ ክፍል የከበረው ከ2006-2010 ሲሆን አላማውም የትን ግንዘቤ ማሳደግ የስነምግባር ለውጥ ለማምጣት ማኅበረሰቡ ተባብሮ ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን እንዲያወግዝ ማድረግ እንዲሁም የሴቶችን ማኅበሮችን ማደራጀት እና ማጠናከር ነበር። ከ1-5 ሚሊዮን በላይ አዋቂዎች እና 575,000 እዳነትን ያካተተውን እቅድ በተለያዩ ባህሪ ቀራጭ ድርጊቶች እንዲሳተፋ ተደርገዋል ይህም ስለ ጉዳዩ ያላቸው ግንዘቤ በተለያየ ደረጃ እነዲያደርግ ወሳኝ ሚና ከመጫወቱ ባሻገር ውጤት ተኩር ለመተግበር የሚያስቸግሩ እና ብዙ ወጭ የሚያስፈልጋቸው የማኅበረሰብ ሥራ ተምሳሌቶች ማግኘት ተችሏል።

- ሁለተኛውም ክፈል የተተገበረው ከ2011-2015 ሲሆን በመሀል በ2013 የተካሄደ ግምገማ እንዳሳየው ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ መቻሉን ነው። ውጤቶቹም የሚያያዙት እቅዱ ያኰረባቸው ማኅበረሰቦች ዘንድ የአመለካከት ለውጥ አንዲኖር አድረጓል። ይህም በሴት ልጅ ግርዛት እንዲሁም ሌላ ጉጂ ባህላዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ብሔራዊም ሆነ ክልላዊ ሕጐች እንዲከበሩ እና ባህላዊ ወይም የጉሳ አለቆተ እነዚህ ህጐች እንዲከበሩ ግፊት አድርገዋል። ሰዎችን ማሰተሳሰር ግንዘቤን ማሳደግ እንዲሁም የጥምረት ሥራ ከተጠቀሟቸው ስልቶች አንድ አንዶቹ ሲሆኑ ይህም እንደ ራዲዮ የመሳሰሉ የመገናኛ ብዙሐንን የመሀበረሰብ አለቃዎችን፣የሕግ አስከባሪዎችን፣እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችን ማሳተፍ ተችሏል። ታላቅ ሚና የተጫወቱት መካከል የሀይማኖት ድርጅቶች የተለያዩ የሀይማኖት ተቋማት የተዋቀሩ ድርጅቶችን መጥቀስ ይቻላል የባህሪ ለውጥ ለማምጣት እና ልምዳችን ለመቀየር ትልቅ አስተዋጾ አርገዋል።

## ብርሀነ ሂዋን

ከ26,000 ከ10-16 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጃችን ያቀፈው እና የመሀበረሰብ አይነት አደረጃጀት ያለው እቅድ በገጠሬቷ ኢትዩጵያ ውስጥ የህፃናት ጋብቻ ለመቀነስ ይጥራል። ብርሃነ ሂዋን ሴቶችን ለቡድን ለማደራጀት ቁሳዊ እርዳታ ለማድረግ / ከብት ወይም በፀሐይ የሚሰሩ ፈየሶች/ እንዲሁም ትምህርታቸውን ሴቶች እንዳያቋርጡ በማድረግ እና የተለያዩ ጉዳዩች ላይ ማኅበረሰቡ ያለውን ግንዘቤ በማሳደግ ሥራውን ይሰራል[32]።

- ከ10-14 ዓመት የሞላቸው በእቅዱ መጨረሻ ትምህርት የመመዝገብ እድላቸው መጨመሩ ታይቷል / (70%)-(96%) /እንደ ትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ ደግሞ እና ሴት ልጅ እንድትማር ካረጉ የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ ዋናው የዚህ ውጤት መንስሄ ናቸው ተብሎ ይታሰባል[33]።

- በተጨማሪም ለመሀበረሰቡ ውስጥ የሚደረጉ ውይይቶች የሴት ልጅ ማኅበሮች እንዲሁም ቤት ለቤት የሚደረጉ የምክር አገልግሎቶች ስለ ሕጻን  ልጅ ጋብቻ ያለውን አመለካከት ለመቀየር እንዲሁም ስለ ስነ ተዋልዶ እና ጤና ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያድግ ማድረጋቸውን የቤተሰብ አባላት ይገልጻሉ[32]።

- ጥናት ያካሄዱ ሰዎችም ከነዚህ ድርጊቶች በኋላ የሴቶች መዳርያ እድሜ ከፍ ሊል መቻሉን ይናገራሉ[34]።

  - ሴቶች በመሀበረሰባ ውስጥ ድጋፍ ሲያኙ ከ12-14 ዓመት የሞላቸው (94%) ሳይዳሩ ይቀራሉ እኩዩቻቸው ግን በድጎፍ ማጣት በዚህ እድሜ ያገባሉ።

  - ሳያገቡ በቆዩበት እና ትምህርት በቀጠሉ ቁጥር ሁለት ትዳር በሚሰጥባቸው ማሕበረሰቦች ውስጥ 15-17 ዓመት የሞላቸው ሴቶች ለግማሽ የመዳር እድላቸው ከሌሎች እኩዩቻቸው ጋር ሲታይ ይቀንሳል።

  - በመሀበረሰባቸው ውስጥ ሴቶችን ማስተማር ዋጋ እንዳለው እንዲሁም የህጻናት ጋብቻ እና ተያያዥ ችግሮቹ የሚነሱባቸው ውይይቶች ሲለመዱ 12-14 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆች በዛ እድሜ ካሉ እኩዩቻቸው ጋር ሲነጻጸር 2/3 የመዳር እድላቸው ይቀንሳል።

  - የተዘረዘሩት ሁሉ ስልቶች በሚተገበርባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ከ15-17 ዓመት የሞላቸው ሴቶች ከሌሎች እኩዩቻቸው ጋር ሲተያዩ በ2/3 የመዳር እድላቸው ይቀንሳል።

## ብሩህ ተስፋ

- በ2016 ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ይህን እቅድ 75000 በላይ ሰዎተነ አሳተፋል ማኅበረሰብ መሰል እቅድም ከ10-19 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆችን በመደገፍ በድህንነት የሚኖሩ የከተማ ወጣቶችን በመደገፍ ግንዘቢያቸውን በማሳደግ የኤች አይ ቪ ሰለባ እንዲይሆኑ፣የትምህርት ውጤታቸው እንዲዳብር እንዲሁም የተሻለ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይጥራል[35]።

- የደህንነት ማህከል ተምሳሌቶችን ለመጠቀም እና መላ መሀበረሰቡን ለማሳተፍ እቅዱ ስለ ግብረ ስጋ እና ስለ ስነ -ተዋልዶ ጤና ውይይቶች በማዘጋጀት፣ሴት ልጆች እና ቤተሰቦቻቸው ሊያገኙአቸው ስለሚችሏቸው አገልግሎቶች በተለየዩ ፕሮግራሞች እንዲሁም ቤት ለቤት በመዘዋወር ግንዛቤ ይሰጣል[32]

- በዚህም ምክንያት የእቅዱ ተሳታፊዎች በሁለት እጥፍ ፍቃደኛ የምክር አገልግሎት እንዲሁም የደም ምርመራ የት ማድረግ እንደሚችሉ ከእኩዩቻቻው ይልቅ ያውቁ ነበር32። በተጨማሪም የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ከብሩህ ተስፋ ባገኙነት ድጋፍ ምክንያት የተሻለ የስነ ፅሁፍ እንዲሁም የሂሣብ ውጤት ሊያስመዘግቡ ችለዋል በፕሮግራሙ ልተሳተፋ ሴት እኩዩቻቸው ጋር ሴተያዩ አብዛኛዎቹ የጤናና አገልግሎት የማግኘት እድላቸው ይጨምራል[48]።

- አሁን እየተካሄደ ያለው ብሩህ ተስፋ ለሁሉም የተሰኘው ፕሮግራም ተጨማሪ 10,500 ሴቶችን በ4 የኢትዮጵያ ከተማዎች ለማቀፍ አቅዷል[35,36]።

## መሠረተ ሕወት[32]

- ይህ ማኅበረሰብ ተኰር ፕሮግራም 230,000 ከ10-24 ዓመት የሞላቸው ሴት ልጆች ላይ ሲያተኩር በይበልጥም ያገቡ ሴቶች ላይ በይበልጥ ይሰራል በተጓዳኝም በሌላ ተመሳሳይ ህቅዱ 130,000 የሚሞሉ ባልዎች ላይ አተኩሮ ይሰራል አላማው ገጠር የሚኖሩ ያገቡ ወጣት ሴቶችን ለመደገፍ የማኅበረሰባዊ ትስስር እንዲኖራቸው እንዲሁም እውቀታቸው እና ችሎታቸው ዳብሮ ያላቸው የስነ-ተዋልዶ እንዲሁም ባጠቃላይ ያላቸውን ጤና እንዲጠብቁ ያደርጋል።

- በፕሮግራሙ የተሳተፉ ሴቶችም እንደሚናገሩት ባሎቻዋውን ባያጋጥምም እነሱ ግን ባለፉት 3 ወራት ተገደው ግብረ ስጋ ግንኙነት አድርገዋል በዚህም በእቅዱ ካልተሳተፉ ሰዎች ወይም ባል እና ሚስት ተሳታፊዎች ጋር ሲተያይ ነው ይህ የሚያሳየውም ባሎች ወይም ጓደኞች ሲሳተፉ ምን ያህል ጾታ ነክ ጥቃቶች እንደሚቀንሱ ያሳያል ነገር ግን ጥናቱን ያካሄዱት እንደሚሉት ጥናቱ ያደላ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የተሳተፉ ሚስቶች በግዳጅ ሰለሚፈጸም ግንኙነት ያላቸው እውቀት ሊጨምር ይችላል።

- ፕሮግራሙ ሚዛናዊ የጾታ ሚና ክፍፍልም በትዳር ውስጥ ለማስፈን ይጥራል፡ ፡ ባልም ሚስትም አብረው በሚሳተፉበት ጊዜ ባለፉት 3 ወራቶች ውስጥ ባል ሚስቱን የማገዝ እድሉ 81% ሚስቶች ብቻ በፕሮግራሙ ውስጥ ሊሳተፉ የእርዳታው መጠን 59% ሲሆን ባልም ሚስትም ሳይሳተፉ ሲቀሩ ደግሞ 33% ነው።

## አዲስ ብርሃን[37]

- ይህ ፕሮግራም ባሎችን እና አሰልጣኞችን በማጣመር ሚዛናዊ የጾታ ግንኙነት እንዲኖር እናኤች አይ ቪን ለመከላከል ይጥራል የመሰረተ ሂወት ተዛማጅ ፕሮግራም ነው።

- የሰለጠኑ ወንድ ለአማካሪዎተ በሳምንት ስብሰባ በማካሃድ ያገቡ ወነዶችን ስለ ጾታ ሰለ ግንኙነቶች ስለ ህፃናት እና ቤተሰብ እንክብካቤ ስለ አደንዛዥ እጽ እና አልኮል ስለ ጾታዊ እና ስለ ጾታዊ እና ስነ-ተዋልዶ ጤና እና ስለ ጥቃት ይለያያሉ።

- በመጨረሻም እንደታየውም ባልና ሚስት አብረው ሲሳተፉ ሚስቶች 18 ጊዜ እጥፍ በሆነ መልኩ በፍቃደኝነት የኤች አይ ቪ ምክር አገልግሎተ እና ምርመራ ማግኘታቸውን እና 8 ጊዜ እጥፍም ባሎቻቸው ስልጠናውን ያልወሰዱ ሴቶች ጋር ሲተያዩ ባሎቻው በቤት ውስጥ ሥራ እንደሚያግዟቸው ታይቷል።

## የወንዶች ደንብ እቅድ [38]

- ይህ ማኅበረሰብ ተኮር እቅድ በአዲስ አበባ ከሚገኙ ወጣቶች ጋር በመሆን ለ6 ወር ያክል ስለ ጉጂ ጾታ ነክ ደንቦች እንዲሁም ተያያዥ የሆኑ ባህርያት የሚያስከትሉትን ጉዳት ፡- እንዲሁም ጤና ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተጽኖችን በተመለከተ አወያይቶአል።

    - ፕሮግራሙ 3 ክፍል ሲኖረው፡-  
      1. በቡድን ስለ መህበረሰባዊ ድርጊቶች መማር  
      2. ማኅበረሰብ አቀፍ ብቻ የሆኑ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ማካሄድ  
      3. ጣልቃ የማይገባባቸው እንቅስቃሴዎች ለቁጥጥር እንዲያመቹ በማካሄድ/ ከጥናቱ በኋላ የዘገየ ድጋፍ ተካሂዶላቸዋል/

- በስተመጨረሻ በስልጠና ቡድኑ የተሳተፉ ወጣት ወንዶች ካልተሳተፉ እኩዩቻቸው ሲነጻጻሩ የጾታ እኩልነትን የሚደግፉ ወንዶችን መመዘኛ ላይ በሁለት እጥፍ ተጨማሪ ነጥብ ሊያገኙ ችለዋል። በመሀበረሰቡ የተሳተፈው ቡድንም የተሻለ እና አመርቂ ውጤት ሊያገኙ ተለዋል።

- በሁለቱም ፕግራሞች የተሳተፉት እንደመለከቱት ክትትል ከተደረበት ቡድን ሲታያዩ ባለፉት 6 ወራተ የትዳር አገራቸውን በኃይል የማጥቃት ሁኔታ እጅጉን ቀንሶል በትምህርትም ስልጠና የተሳተፈውም ቡድን እና እንዲሁም በመህበረሰብ ተኮር ቡድን የተሳተፉት በትዳር አጋር የሚሰነዘሩ ጥቃቶች ከ 36% ወደ 16% ዝቅ ሲሉ ማኅበረሰብ ተኮር እንቅስቃሴ ብቻ ሲያደርግ የነበረ ቡድን ከ 36%ወደ 18% ቀንሶል ክትትል ብቻ ሲደረግበት የበረ ቡድን ግን 7% ወደ 14%ጥቃቱ ሊጨምር ችሏል።

- ወጣት ወንዶች ያጋጠማቸውን መልካም የባህሪ ለውጥ ከፕሮግራሙ ጋር በቀጥታ ይያያዛል ሲሉ አብኛውዎቹ ሴቶችም የትዳር አጋሮቻቸው መልከም የባሕሪ ለውጥ እንዳሳዩ ይናገራሉ።

## ጐጂ ባህላዊ ልምዳቸን እና በሴቶቸ ላይ የሚፈጸም ጥቃትን መዋጋት [39]

- ሴቶቸን የመከታተሉ ቡድኖቸ በሆፍላ ወረዳ ለመመስረት ሴቶቸ ላይ ሰለሚፈጸም ጥቃት ግንዛቤ በመፍጠር፣ሴቶቸን ከአፍላ ወይም ከልጆቸ ጋብቻ ለመጠበቅ ከጾታ ጥቃት ለመጠበቅ በፍቺ ግዜ ሴቶቸ በአግባቡ እንዲካሱ በማድረግ ብድር ለሚያስፈልጋቸው የብድር አገልግሎት በማመቻቸት እና የማኅበረሰብ አለቃዎቸን ለማሳተፍ ይጥራሉ።
    - እንዚህ ቡድኖቸ ከዚህ ቀደም የተመሰረቱ እና ወጣት ወንዶቸን ወይም ወጣት ሴቶቸን ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ማኅበሮቸን ድጋፍ ሰተዋል። / ይህ ስል በአንድ አንድ ሰፍሮ ተሰርቷል/

- ከመረጃ ምንጮቸ እንዳወቁት እነዚህ የሴቶቸ ክትትል ቡድኖቸ እና የመንግስት አካላት እንቅስቃሴ የሕጻናት ጋብቻ በእጅግ ሊቀንስ ቸለዋል። በተጨማሪም እነዚህ ቡድናቸ ማኅበረሰቦቸ ያላቸው ግንዛቤ እና ለሴቶቸ ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት እንዲጨምር አድርጓል። በተጨማሪም ታዳጊ እና ወጣት ወንዶቸ ሰለ ጾታ ጫና እና በመሀበረሰቡ ውስጥ ያለውን ክስተት በይበልጥ መረዳታቸው እና በሳል እና የተማረ ሴት መግባት ያለውን ጥቅም ተረድተዋል። እነዚህም የቁጥጥር ቡድኖቸም ህጋዊ እርምጃ መውሰዳቸው እንደ ድብቅ ጋብቻ የመባሰሉትን ጐጂ ሚስጥራዊ ድርጊቶቸ እንዲቀንሱ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።

- የፕሮግራሙ ስኬት የተለያየ አቀራረብ በማካተቱ ቀጣይ ግንኙነት መመስረቱ ፦ ወሳኝ ድጋፍ መስጠቱ ያልተቋረጠ የማኅበረሰብ ክትትል መኖሩ እና የሴቶቸ መብት ተሟጋቸ ማፍራቱ ጋር ይያያዛል።
    - ፕሮግራሙ ስኬት የተለያዩ አቀራረብ በማካተቱ፦
    - ቀጣይ ግንኙነት መመስረቱ፦ ወሳኝ ድጎፍ መስጠቱ፦ ያልተቋረጠ የማኅበረሰብ ክትትል መኖሩ እና የሴቶቸ መብት ተሟጋቸ ማፍራቱ ጋር ይያያዛል።
    - ፕሮግራሙ መሀበረሰቡ ይመለከተናል ስሜት ተሰምቶት ጤነኛ ትብብርና ትስስር እንዲኖር አድርጓል።
    - የሴቶቸ ክትትል ቡድኖቸ ለተጋላጭ ሰቶቸ መከታ በመሆናቸው ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር ወሳኝ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል።
    - ያለማቋረጥ የሚደረግ ክትትልም የክልሉ ቤተሰቦቸ እና የመንግስት ሠራተኞቸ ዳባም እንደ አስፈላጊነቱ ሰልጠነው ሴቶቸ እንዲማሩ ለማበረታታት ያለ እድሜ ጋበቻን ያወግዛሉ።

## ወደ ዳበረ አካዳሚ እና የጾታ የስነተዋልዶ ጤና ለታዳጊ ሴቶቸ /ተስፋ/[39]

- የሴቶቸ ደህንነት ለማሻሻል የታሰበ ፕሮግራም ሦስት ክፍሎቸ አሉ። አንደኛው የጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ሲያተኩር ; ሁለተኛው ክፍል የአካዳሚ አቅምን ለማሳደግ ሲጥር ;ሦስተኛው አካል ደግሞ የጾታ እና የስነ ተዋልዶ እና አካዳሚ ላይ ያተኮረ ስራ ይሰራል / የክትትል ጐርፕም ከጥናቱ በኋላ ድጋፍ ያገኛል።

- ፕሮግራሙም ከ 70%-80%ያለ እድሜ ጋብቻ መቀነሱን እና በግዳጅ የሚፈጸም ጋብቻ መጥፋቱን አይቷል ትልቅ ድጋፍ ያበረከተውም የመንግስት ተሳትፍ እና በትምህርት ቤት ውስጥ የክትትል ስራ መስራቱ ነው። እንደዚህ አይነት ማኅበረሰብ እና መንግስትን ያጣመሩ እንቅስቃሴዎቸ ስለ ያለ እድሜ ጋብቻ ማኅበረሰቡ ያለውን ግንዛቤ ሊያሳድግ ቸለዋል በተማሪም - በይበልጠ ሴት ልጆቸ በይበልጥ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል።

- ስኬታማነቱ የሚያያዘው በጥንቃቄነገግራሙ መተነጽ እና መተግበሩ ማኅበረሰቡ ይመለከተኛል ብሎ በማሰብ እንዲቆረቆር በማድረጉ ነው ይህም ሁኔታ ተሰሜነት ካላቸው ሰዎቸ ጋር በተለያዩ መደቦቸ በመስራት ማኅበረሰቡ እርሰ በእርስ እንዲማር በማስቻሉ ነው። በማኅበረሰቡ ውሰጠ ያሉ ለረዥም ጊዜ የቆዩ ትስስሮቸ መኖራቸው በፕሮግራሙ ታሳቢ ለመሆን በምን መልኩ ማኅበረሰቡን መቅረብ እንደሚሀቻል በማመዛዘን እና ከእለት ተለት ኑሯቸትው ጋር የሚቆራኝ መልከቶቸ አስቦ በማስተላለፍ ስኬታማ ለመሆነ ተቸሏል። ይህ አቀራረብም የሀይማኖት አባቶቸ እና ያገቡ የሴት ማኅኖቸን በመሳብ መልእክቱን እንዲያስተላለፉ ረድቷቸዋል። በመጨረሻም ይመለከተኛል ያሉ ስሜት እንዲዳብር የሰለጠኑትን በተራቸው ሌሎቸን እንዲያሰለጥኑ በማድረግ ድሮ ያለ እድሜ ጋብቻ ይደግፋ የነበሩትን ዛሬ ግን እንዲቃረኑት ለማድረግ ተቸሏል።

*Effectiveness is linked to the program's careful design and implementation that worked with a focus of integration to foster local ownership.*

## መረጃዎች ለአቃቀም የሚይከበዱ ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ እና ሊቋረጥ የሚችል የወሊድ መቆጣጠሪያ አቀርቦ ተምሳሊት [40,41]፡፡

- ይህ ሙከራ 10 ስፍራዎች ላይ ከ2014 -2015 ተደርጎ:
  1. የመተከል ወይም የሚቀበር የወሊድ መቆጣጠሪያን መስጠት የሚያችል እና ወጣቶችን የሚስብ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስልጠና በመስጠት አገልገሎቱን ማቋረጥ ሲያስፈልገም ተገቢውን አገልግሎት እና መመረዝ እንዳይኖር ክትትል በማድረግ፣
  2. አሰልጣኞች ለሌሎች ስለሚሰጠት ሥልጠና መዳበርያ ስልጠናዎች በመስጠት/ ለምሳሌ የተሳሳተ አመለካከት ወይም እምነትን በማቃናት / እንዲሁም ለረዥም ጊዜ የሚያገለግሉ እና ሊቋረጡ የማችሉ የወሊድ መቆጣጠሪያ ስልቶች የጤና እንከን እንደማይፈጥሩ ለማሳወቅ ወደ ሚሰጡበቸው ስፍራ ሰዎችን ለመላከ
  3. የድጋፍ ክትትል ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ይህ የተሞከረ
- የአገልግሎት ተምሳሌት የረዥም ጊዜ የሚያገለግሉ እና ሊቋረጡ የሚችሉ የወሊድ መቆጣጠርያዎችን ፕግራሙ ያተኮረባቸው ስፍራዎች ካልተሰሪባቸው ስፍራዎች ሲታዩ ይበልጠ ተጠቃሚዎች እንዳሉ ታውቋል ጥናቱ ያካሄድ ሰዎች እንደሚሉት ያልወለድ ሴቶችም በይበልጥ የወሊድ መቆጣጠርያ መጠቀም መጀመራቸውን ተናግረዋል፡፡
- ጥናቱ በተካሄደበት ግዜ 63% የሚቆጠህሩት ሴቶች ፕሮግራሙ በተካሄደበት ስፍራ ላይ 81% ደግሞ ለመጀመሪያ ግዜ ለረዥም ግዜ የሚያገለግል እና ሊቋረጥ የሚችል የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ ሴቶች እስከአሁን እንዳልወለዱ ይናገራሉ፡፡
- ይህ አሰራር ስልት ያስገኘው ከፍተኛ ውጤት ከፍ ባለ መልኩ በ66 ወጣት ተኮር የአገልገሎት መስጫ ስፍራዎች በአማራ ክልል ለትግራይ ክልልም 62 ተመሳሳይ ስፍራዎች ከ2015-2016 በአገልገሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

## የጤና ባለሙያዋችን የሃይማኖች አባቶችን እና የመገናኛ በዙኃኖችን ለመጠቀም ሰዋች ስለ ያለ እድሜ ያላቸውን ግንዛቤ መለወጥ[42]

- የጤና ባለሙያዋች ሰለ ስነ ተዋልዶ ስለ ወሊድ መቆጣጠር እንዲሁም ሰለ ወር አበባ ማስተማራቸው ሰዎች ያላቸውን አስተሳሰብ በእጅጉ አሰተዋጽዎ አድርጓል ይህም በገጠር አካባቢ ይታያል፡፡
- ያለ እድሜ ጋብቻ እና ወሊድ ሰለሚያስከትሉተም የጠና እንከን ማስተማራቸው ሰዎች ስለ ፊስቱላ የእናቶች ሞት እውቅና አሳድጓል፡፡
- በጤና ባለሙያዋች ለሴት ማኅበረ መሬዎች የሚደረጉ እነቅስቃሴዎች ስራ ባሉ የሬድዮ ቅስቀሳ ፕሮግራሞች እና ተመሳሳይ ግንዘቤ አስጨባጭ እነቅስቃሴዎች ጋር በመዳመር ሰዎች አንድ ሰው አንድ ሰው 18 ዓመት ሲሞላው ብቻ ለአቅመ ጋብቻ መድረሱን እና ከዛ በፊት የሚፈጸም ጋብቻ እንደሚያስጠይቅ ሰዎች እንዲረዱ አድርጓል፡፡ ያለ እድሜ ጋብቻን በተመለከተ ታላቆች ምክር ይልቅ አዲሱን ህግ ሰዎች ይበልጥ እንደሚያከብሩ ታውቋል፡፡
- የኢትዩተያ ኦርቶዶክሰ ቤተ-ክርስትያን የሀገሬቱ ዴንብ እንደሚፈቅደው ሴት ልጆች አሰራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው መዳር እንደሌለባቸው መልክቱን ታስተላልፋለች፡፡ ነገር ግን እንዳንድ ቄሱች ከዚህ ጋር የሚቃረን ባህሪ አንዳንዴ ይስተዋልባቸዋል፡፡
- የጤና ባለሙያዎች ክትትል ያለ እድሜ ጋብቻ እንዲቀንስ አሰተዋጾ አድርጓል፡፡
- ስለዚህም ሰዎች ሴት ልጆች ለትዳር ደርሰዋል ተብሎ የሚታሰብበተ ጊዜ ይህ ነው ብሎ ማሰብ መጀመራቸው በቅርብ እየታዩ ያሉት መሻሻሎች እና በቀበሌ እና በወረዳ ደረጃ ያለውን ክትትል ጋርም ተያያዥነት አለው፡፡

*During the study period, 63% of women who were served at intervention sites, and 81% of woman who accepted a LARC method for the first time, had not yet had a child.*



## ማስጠንቀቂያ

ለወጣቶች አመቺ የሆኑ አገልግሎቶችን በተመለከተ ብዙ ጉጉት ቢስተዋልም መረጃዎች ግን የሚያመላክቱት ግን የጾታ እኩልነትን ለመጨመርም ሆነ የሴቶች ስነተዋልዶ እና የጾታ ግንኙነት ለማሻሻል ምንም አስተዋጾ እንደሌላቸው ነው፡ ፡ አንድ ጥናት እንዳገኘው ለወጣት አመቺ አገልግሎቶችን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ነው።

ምክንያቱም ከሴት ልጆች ወይም ሴቶች መካከል 7% ብቻ ወንድ ልጆች ደግሞ 8% ብቻ እንዳሉ (12-24 እድሜ የሞላቸው) ስለ ተጠቀሱት አገልግሎቶች ያቃሉ እናም በዚህ ምክንያት ተጠቃሚዎቹ ለሴት ወጣት ከ2% ያልዘለለ ለወንድ ወጣት ደግሞ 4% ያልዘለለ የተጠቃሚዎች ቁጥር ተመዝግቧል። ነገር ግን ድንገት እነዚህን ስፍራዎች ከመደበኛ የጤና ጣቢያ ሳይለያቸው ነገር ግን ጉብኝተውት ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል። (37% ሴቶች 39% ወንዶች)43. ሌላ ጥናት ደግሞ እንዳመለከተው እነዚህ የጤና ማህከሎችን ያለው የመጠቀም ሁኔታ 39% ሲሆን ይህም ከተለመደው የጤና ጣቢያ ግልጋሎት እግጅ በጣም ተቀራራቢ ነው44። ይህ የጤና ጥናት እንደሚያመለክተው ባደረጃጅታቸው በስራ ሂደታቸው እና ሽፋናቸው ጥራታቸው ሲመዘን 54%፣ 42% እና 49% አስመዝግበዋል፤ ከሚጠበቀው 75% በታች በመሆን እነዚህ ለወጣት አመቺ መዓከሎች ከደረጃ በታች ተፈርጀዋል45፡ ፡ እነዚህን በይበልጥ መጠቀም ጥራታቸውን ማሳደግ እንዲሁም የተሻሉ ፕሮግራሞችን በማመቻቸት ለወደፊቱ የወጣቶች የጤና ጥያቄዎች ለመመለስ እና ለመሸፈን አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታሰባል።

# መዝግያ

ኢትዮጵያ ህዝቧ በፍጥነት እያደገ ያለ አብዛኛዎቹ ዜጎችም ወጣቶች የሆኑ ከተሞችዋ  በፍጥት እያደጉ ያሉ ሰፊ ሀገር ናት። ኢትዮጵያ የከበረ ባህል ያላት የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏት እነርሱም የራሳቸውን ቋንቋ የሚናገሩባት የራሳቸው ባህል ያኗኗር ዘይቤ ይዘው የሚኖሩባት ናት፤ እንደዚህ የከበሩ የባህል ቅርጾች ቢኖራትም በዛው ልክ ከመወለድ አንስቶ እድሜ ልክ የሚቆዩ እና የፆታ እኩልነትን የሚሸሩ ጎጂ ባህላዊ ልምዶች እና ደንቦች አሏት። ወንድና ሴት መሐል ያሉት ልዩነቶች በወጣትነት ጊዜ ይበልጥ ይጎላሉ ፆታ ላይ የተመሰረቱ መድሎዎች ትምህርት በመማር ላይ የጋብቻ እድሜ ላይ የተከፈለም ሆነ ያልተከፈሉ ስራ ላይ እንዲሁም ጥቃትን በተመለከ የሚያውለው ተጽኖ ይታያል ነገር  ግን ኢትዮጵያ ጠንካራ ፖሊስ እንዲሁም ህጎች ለማጽደቅ እነዚህን ተጽዕኖዎች ለመቅረፍ እየጣረች ነው። በተጨማሪም በቅርብ የሴቶችም ሆነ የወጣቶች አመራር እየጨመረ መጥቷል። በሀገሪቱም ያሉ ህጎች የመንግስትም እና የበጎ አድራጎት ድርጅት ቅንብር ተመቻችቷል።

የመንግስት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጥረት ፆታ ተኮር መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ በወጣነት ግዜ በተለያዩ ቦታዎች የጾታ እኩልነት እንዲሻሻል አድርጓል። ለምሳሌ ያለእድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ባለፉት ዓመታት እጅጉን ቀንሷል። እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት በተመለከተ ያሉ ልዮነቶች እየጠበቡ መጥተዋል።

በተለያዩ ስፍራዎች መሻሻል ቢታዩም ያልተገቱ እንቅፋቶችም ይስተዋላሉ፤ ብዙ የወጣትነት ሕይወት ምዕራፎች ፕሮግራም ለሚያወጡ እና ውሳኔ ለሚወስዱ አካላት የተዳፈነ ነው። ይህም በቂ መረጃ በአንዳንድ ስፍራዎች አለመኖሩን ነው።

እንደምሳሌም ስራን እና መተዳደሪያን የአእምሮ ጤና ሱስን አመጋገብን ስደትን በሐገር ውስጥም ሆነ በውጭው አለም የሚደረግ ህገወጥ ዝውውርም እንዲሁም ጾታ ነክ ወይም ሌላ ጥቃቶችን መጥቀስ ይቻላል። መፍትሔም ለማግኘት ሁሉንም የማህበረሰብ አካላት ያጣመረ ወጥ የውሳኔ እና የመተግበር ሂደት ያስፈልጋል። የፖለቲካ ተቋማት በእነዚህ ነጥቦች ላይ ቢያተኩሩም ምርምር አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች ኋላቀር ናቸው።

በተጨማሪም 80% ነዋሪዎችም ገጠር በመኖራቸው ሀገሪቷ ህግ እና ደንቦችን በተመለከተ ግንዛቤም ሆነ አቅርቦቱ የተወሰነ ነው። በይበልጥም ራቅ ያሉ እና ለመሄድ የሚቻሉባቸው ስፍራዎች አዳጋች ይሆናሉ፡ ፡ በመጨረሻም በአመራር ቦታ ላይ ያሉ ወጣቶች ቁጥር ቢጨምርም አብዛኛዎቹ መጣቶች እነሱን ስለሚመለከቱ ደንቦች ያላቸው እውቀት ጥልቅ አይደለም። ወጣት ኢትዮጵያዊያን ውሳኔ በሚወሰድባቸው የተለያዩ ደረጃዎች ያላቸው ተሳትፎ ውስን ነው። እነዚህ ችግሮች የህዝብ ቁጥርዎ አመርቂ ሊሆን በተቃረበበት ጊዜ እነዚህ ጉዳዮች አንገብጋቢ ይሆናሉ። ምክንያቱም የዛሬን እና የወደፊት ወጣቶችን አቅም መጠቀም ባስቸኳይ መቻል አለባት።

ኢትዮጵያ የጾታ እኩልነትን በተለያዩ መስኮች አሻሽላለች የዚህም ስኬት ምክንያት በወጣትነት ጊዜያቸው ወንድ እና ሴቶች ላይ አትኩራ በመስራትዋ ነው። በወጣትነት ጊዜ የፆታ እኩልነትን በማስፈን የሚደረጉ ጥረቶቹ መጨመር SDGS ለማሳካት የህዝብ ቁጥር የሚሰጣትን ቁጥር ለመጠቀም እና ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ጤናማ አመርቂ እና የተሟላ ሕይወት እንዲኖሩ ታላቅ አስተዋጽዖ አለው።

## REFERENCES


[1] Oljira, Lemessa. (2016).National Adolescent and Youth Strategy: 2016-2020 Federal Democratic Republic of Ethiopia, Ministry of Health.

[2] United Nations, Department of Economic and Social Affairs, Population Division (2015). World Population Prospects: The 2015 Revision, Key Findings and Advance Tables. Working Paper No. ESA/P/WP.241. https://www.populationpyramid.net/ethiopia/2017.

[3] Hailemariam, A., Gurmu, E., & Solomon, A. (2017). *The Demographic Dividend: Imperative for Ethiopia's Transformation* (Rep.). Addis Ababa: Ethiopian Academy of Sciences.

[4] Wamsley, L. (2018, October 25). Ethiopia Gets Its 1st Female President. Retrieved from https://www.npr.org/2018/10/25/660618139/ethiopia-gets-its-first-female-president

[5] Ethiopia's Abiy gives half of ministerial posts to women. (2018, October 16). Retrieved from https://www.bbc.com/news/world-africa-45881004

[6] *National Adolescent and Youth Health Strategy: Baseline Statistics* (Rep.). (2017). Addis Ababa: Ethiopia Ministry of Health.

[7] Hafkin , N. J. (2016). National Assessments on Gender and Science, Technology and Innovation: A review of four country assessments from East Africa: Ethiopia, Kenya, Rwanda and Uganda. National Assessments on Gender and Science, Technology and Innovation: A review of four country assessments from East Africa: Ethiopia, Kenya, Rwanda and Uganda. Women in Global Science and Technology .

[8] Trines, S. (2018, November 15). Education in Ethiopia. Retrieved from https://wenr.wes.org/2018/11/education-in-ethiopia

[9] Ethiopian University entrance point NEAEA 2017 Grade 12. (2018, November 26). Retrieved from https://www.esetube.com/ethiopian-university-entrance-point-neaea-2017/

[10] Cherinet, H., & Mulugeta, E. (2003). A Profile on Gender Relations: Towards Gender Equality in Ethiopia. A Profile on Gender Relations: Towards Gender Equality in Ethiopia. Sida.

[11] Mani, Subha, John Hoddinott, and John Strauss. 2010. "Long-Term Impact of Investments in Early Schooling: Empirical Evidence from Rural Ethiopia." Discussion Paper Series 00981, International Food Policy Research Institute, Washington, DC. Retrieved from https://pdfs.semanticscholar.org/18d9/fbd2497480ae8e92836cde172611eb41e362.pdf.

[12] Jones, N., Tefera, B., Emirie, G., Yadete, W., Gezahegne, K., Tilahun, K., & Birhanu, K. (2017). *Exploring Ethiopian adolescents' gendered experiences and perspectives* (Rep.). London: GAGE.

[13] Girls Not Brides. (n.d.). Ethiopia - Child Marriage Around The World. Girls Not Brides. Retrieved from https://www.girlsnotbrides.org/child-marriage/ethiopia/

[14] Central Statistical Agency (CSA) [Ethiopia] and ICF. 2016. *Ethiopia Demographic and Health Survey 2016*. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF.

[15] Erulkar, A. (2013). Early Marriage, Marital Relations and Intimate Partner Violence in Ethiopia. International Perspectives on Sexual and Reproductive Health, 39(01), 006–013. doi: 10.1363/3900613

[16] Maternal mortality ratio (modeled estimate, per 100,000 live births). (0AD). Retrieved from https://data.worldbank.org/indicator/SH.STA.MMRT?locations=ET&most_recent_value_desc=true

[17] Erulkar, A. (2013). Early Marriage, Marital Relations and Intimate Partner Violence in Ethiopia. International Perspectives on Sexual and Reproductive Health, 39(01), 006–013. doi: 10.1363/3900613

[18] Erulkar, Annabel, Girmay Medhin, and Lemi Negeri. 2017. "The Journey of Out-of-School Girls in Ethiopia: Examining Migration, Livelihoods, and HIV." Addis Ababa: Population Council.

[19] UNFPA. (2013). *Motherhood in Childhood: Facing the Challenge of Adolescent Pregnancy . Motherhood in Childhood: Facing the Challenge of Adolescent Pregnancy*. New York, NY.

[20] Erulkar, A., & Ferede, A. (2009). Social Exclusion and Early or Unwanted Sexual Initiation Among Poor Urban Females in Ethiopia. INTERNATIONAL PERSPECTIVES ON SEXUAL AND REPRODUCTIVE HEALTH, 35(4), 186–193.

[21] Boyden , J., Pankhurst, A., & Tafere, Y. (2013). Harmful Traditional Practices and Child Protection: Contested Understandings and Practices of Female Child Marriage and Circumcision in Ethiopia. Harmful Traditional Practices and Child Protection: Contested Understandings and Practices of Female Child Marriage and Circumcision in Ethiopia. London: Young Lives.

[22] Sully, E., Dibaba, Y., Fetters, T., Blades, N., & Bankole, A. (2018). Playing it Safe: Legal and Clandestine Abortions Among Adolescents in Ethiopia. Journal of Adolescent Health, 62(6), 729–736. doi: 10.1016/j.jadohealth.2017.12.015

[23] *HIV Prevention in Ethiopia National Road Map 2018 - 2020* (Rep.). (2018). Addis Ababa: Federal HIV/AIDS Prevention and Control Office.

[24] Jones, N., Gupta, T., & Tefera, B. (2015). Evaluation of Norway's support to women's rights and gender equality in development cooperation: Ethiopia Case Study Report. Evaluation of Norway's support to women's rights and gender equality in development cooperation: Ethiopia Case Study Report. Norwegian Agency for Development Cooperation.

[25] 28 Too Many. (2018). *Ethiopia: The Law and Fgm . Ethiopia: The Law and FGM*. Retrieved from https://www.28toomany.org/static/media/uploads/Law%20Reports/ethiopia_law_report_(july_2018).pdf.

[26] Jones, N., Presler-Marshall, E., Baird, S., Hicks, J., Emirie, G., Yadete, W., Alemayehu, Y., Bekele, B. and Kifle, E. (2019) *Adolescent bodily integrity and freedom from violence in Ethiopia. A report on GAGE Ethiopia baseline findings. London: Gender and Adolescence: Global Evidence*

[27] Bekele, A. B., Aken, M. A. G. V., & Dubas, J. S. (2011). Sexual Violence Victimization Among Female Secondary School Students in Eastern Ethiopia. Violence and Victims, 26(5), 608–630. doi: 10.1891/0886-6708.26.5.608

[28] Pankhurst, A., Crivello, G., & Tiumelissan, A. (2016). *Children's Work in Family and Community Contexts: Examples from Young Lives Ethiopia. Children's Work in Family and Community Contexts: Examples from Young Lives Ethiopia.* London: Young Lives.

[29] The Ethiopian Urban Migration Study 2008: The Characteristics, Motives and Outcomes of Migrants to Addis Ababa (Rep. No. 55731-ET). (2010). Washington D.C.: World Bank.

[30] Erulkar, Annabel, Girmay Medhin, and Lemi Negeri. 2017. "The Journey of Out-of-School Girls in Ethiopia: Examining Migration, Livelihoods, and HIV." Addis Ababa: Population Council.

[31] Tesfaye, A. (2017). Child Rights Protection in Ethiopia: Critical Analysis of the Statutory Rape Provisions of the Criminal Code and Their Application. Beijing Law Review, 8, 499-525. https://doi.org/10.4236/blr.2017.84028

[32] Marcus, R., Gupta-Archer, N., Darcy, M., & Page, E. (2017). *GAGE Rigorous Review: Girls' clubs, life skills programmes and girls' well- being outcomes* (Rep.). London: GAGE.

[33] Erulkar, A. S., & Muthengi, E. (2009). Evaluation of Berhane Hewan: A Program to Delay Child Marriage in Rural Ethiopia. International Perspectives on Sexual and Reproductive Health, 35(01), 006-014. doi:10.1363/3500609

[34] Building an Evidence Base to Delay Marriage in Sub-Saharan Africa. (0AD). Retrieved from https://www.popcouncil.org/research/building-an-evidence-base-to-delay-marriage-in-sub-saharan-africa.

[35] Biruh Tesfa ("Bright Future"). (0AD). Retrieved from https://www.popcouncil.org/research/biruh-tesfa-safe-spaces-for-out-of-school-girls-in-urban-slum-areas-of-ethi

[36] Biruh Tesfa to Scale-Up, Targeting Pivotal Population of Vulnerable Girls in Ethiopia. (2019, January 28). Retrieved from https://www.popcouncil.org/news/biruh-tesfa-to-scale-up-targeting-pivotal-population-of-vulnerable-girls-in

[37] Addis Birhan ("New Light"). (n.d.). Retrieved from https://www.popcouncil.org/research/addis-birhan

[38] Pulerwitz J, Martin S, Mehta M, Castillo T, Kidanu A, Verani F, Tewolde S. Promoting Gender Equity for HIV and Violence Prevention: Results from the Male Norms Initiative Evaluation in Ethiopia. Washington, DC: PATH; 2010.

[39] Jones, N., Tefera, B., Presler-Marshall, E., Gupta, T., Emirie, G., Gebre, B., & Berhanu, K. (2016). *What works to tackle child marriage in Ethiopia: A review of good practice* (Rep.). London: UNICEF & Overseas Development Institute.

[40] Where We Work: Ethiopia. (0AD). Retrieved from https://www.e2aproject.org/countries/ethiopia/

[41] Evidence to Action Project / IFHP . (2017). Testing a Service-Delivery Model for Offering Long-Acting Reversible Contraceptive Methods to Youth in Ethiopia. Testing a Service-Delivery Model for Offering Long-Acting Reversible Contraceptive Methods to Youth in Ethiopia. Washington D.C..

[42] Early marriage in Ethiopia: The role of gendered social norms in shaping adolescent girls 'futures. Nicola Jones, Bekele Tefera, Janey Stephenson, Taveeshi Gupta and Paola Pereznieto. December 2014

[43] Jain, A., Ismail, H., Tobey, E., and Erulkar, A. 2017. "Understanding Adolescent and Youth Sexual and Reproductive Health-seeking Behaviors in Ethiopia: Implications for Youth Friendly Service Programming," Research Report. Washington, DC: Population Council, The Evidence Project.

[44] Helamo D, Kusheta S, Bancha B, Habtu Y, Yohannes S (2017) Utilization and Factors Affecting Adolescents and Youth Friendly Reproductive Health Services among Secondary School Students in Hadiya Zone, Southern Nations, Nationalities and Peoples Region, Ethiopia. Int J Pub Health Safe 2: 141.

[45] Mulugeta, B., Girma, M., Kejela, G., Meskel, F. G., Andarge, E., & Zerihun, E. (2019). Assessment of Youth-Friendly Service Quality and Associated Factors at Public Health Facilities in Southern Ethiopia: A Facility-Based Cross-Sectional Study. BioMed Research International, 1-11. doi:10.1155/2019/969627.

[46] Erulkar A, Ferede A, Ambelu W, et. al. 2010. *"Ethiopia Young Adult Survey: A Study in Seven Regions,"* Addis Ababa: Population Council and UNFPA, September, 2019.

[47] Ketema H, Erulkar A. 2018. *"Married adolescents and family planning in rural Ethiopia: Understanding Barriers and Opportunities,"* African Journal of Reproductive Health, 22 (4) 27.

[48] Erulkar A, Medhin G. 2017. *Evaluation of a girls' safe spaces program to improve educational outcomes and health service utilization in Ethiopia*, Girlhood Studies 10, no. 1: 107-125.

www.geastudy.org @geastudy